በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

የተሰጠ መግለጫ

የካቲት 26, 2007ዓ.ም

## <u>የየካቲት ገጽታዎች፣ የእኛና የነርሱ ለየቅል።</u>

የካቲት ወር ለኢትዮጵያውያን ታሪካዊ ወር ነው። በበጎም በመጥፎም የሚዘከሯቸው ዕውነታዎች አሉ። ፋሺስት ጣሊያን በእብሪት አገራችንን ወሮ ቅኝ ተገዢዎች ሊያደርገን በመፈለግ ባካሄደው የግፍ ጦርነት ከሰሜኑ የአገራችን ግዛት ወደ መሐል በዘለቀበትና የአገሪቱን መዲና አዲስ አበባን በተቆጣጠረበት ወቅት የድል ነጋሪት ሊያስጎስም ነዋሪዎቿን ሰብስቦ የፉከራ ዲስኩር ሲያሰማ በነበረው የጣሊያን ጦር መሪ ላይ ለነፃነታቸው ቀናኢ የነበሩት ምገስ አስገዶምና አብርሃ ደቦጭ በወኔ ተሞልተው ቦንብ ጣሉበት። በዚህ ሰበብ ከሞት የተረፈው የፋሺስቱ ጦር ጄኔራል ግራዚያኒ ወታደሮቹ ያለርህራሄ መትረየስ በሕዝቡ ላይ እንዲያርከፈክፉ አዘዘ። በአካፋና በዶማም ሳይቀር ጭፍጨፋው ቀጥሎ ሰላሳ ሺህ የሚሆኑ ወገኖቻችን አለቁ። ስድስት ኪሎ የሚገኘው የሰማዕታት ሐውልት ቆሞ ግፉን የሚናገር ሆኗል። ይህ ፋሺስት ቀደም ብሎ በተለያዩ የጦር ውጊያ ግንባሮች ላይ መርዘኛ ጋዝና የኬሚካል መሳሪዎችን በዜጎቻችን ላይ ተጠቅሟል። በነገራችን ላይ በ2012(2004ዓ.ም) በጣሊያን ባንድ ትንሽ መንደር አፍሌ (Affile)በሚባል ቦታ ለዚህ ፋሺስት ጄኔራል ሐውልት ሊሰራለት ሲጀመር አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ከአገር ውጪና በአገር ውስጥ ተቃውሞአቸውን አሰምተዋል። በአዲስ አበባ የተካሄደውን የአገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ተቃውሞ የኢትዮጵያና የሕዝቧ ጠላት የሆነው ወያኔ ለፋሺስቱ ሥርዓት ርዝራዦች ጥብቅና ቆሞ የተቃውሞውን ሰልፍ አኮላሽቷል፤ ቅጥረኝነቱም ገሃድ ወጥቷል። ለአገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ግን የየካቲት 12 የሰማዕታት ቀን የታሪካችን አካል ምን ጊዜም የምናከብረውና ለትውልድ የምናስተላልፈው ይሆናል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው የመጀመሪያው የፋሺስት ጣሊያን ወራሪ ኃይል በደግማዊ ምንልክ በተመራው የኢትዮጵያ ጦር ድባቅ መመታቱ ነው።

ድሉ በፋሺስት ጣሊያን ላይ ቢሆንም አይዞህ ባዮቹና አምሳያዎቹ ቅኝ ገዢዎች ቅስማቸው ክፉኛ ተሰብሯል።የአድዋ ድል በቅኝ ግዛት ሥር ይማቅቁ ለነበሩ  አፍሪቃውያን በተለይ ለጥቁር ሕዝቦች በአጠቃላይ ለነፃነት ተጋድሎ በፈር ቀዳጅነቱ ቀዳሚውን የክብር ስፍራ ይዟል። በቅርቡ የአድዋ በዓልን አስመልክቶ ለአንዳንድ የአፍሪቃ አገር ተወካዮች ከሚዲያ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሩዋንዳና የጋና ተወካዮች የአድዋ ድል የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የመላው አፍሪቃና የጥቁር ሕዝቦች ድል እንደሆነ ገልጸዋል። በተለይም የጋናው ተወካይ የየካቲት 23 ቀን 1888ቱ የአድዋ ድል በመላው አፍሪቃ አገሮች እንዲከበር በጉዳዩ ላይ ውይይት እንዲካሄድ ለአፍሪቃ አንድነት ድርጅት (AU) አገራቸው ጋና በአጀንዳ እንዲያዝ እንደምትጠይቅ ከመግለጻቸውም ሌላ ይህ የአድዋ ድል ለወጣት ጋናውያን በት/ቤት በካርኩለም( በሥርዓት ትምህርት) ውስጥ ተካቶ እንዲማሩ የተደረገ መሆኑን ገልጸዋል። በጎረቤት አገር ኬንያም የአድዋ ድል ታሪክ በት/ቤት ለተማሪዎች በትምህርትነት ይሰጣል።አፍሪቃውያን የጋራ እሴቶቻቸውን በማስከበር በጋራ ለመበልጸግና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን መቋቋም እንደሚያሻ የአድዋ ድልና በዓል የሚያመላክተው አንድምታ ታላቅ ነው።ቅኝ ገዢዎች የአህጉሩን የተፈጥሮ ሀብት እንደልባቸው እንዳይዝቁ ኢትዮጵያውያን መሰናክልና መጥፎ አርአያ ሆነውብናል ብለው ጥርስ እንደነከሱብን እዚህ ወቅት ላይ ደርሰናል። ከመካከላችን የበቀሉ ዘረኞችንና አገር ሻጮችን በሥልጣን ላይ አስቀምጠው ሕዝቡን የሚያተራምሱበት ዋነኛው ሰበብ ይኸው የየካቲት 23ቀን 1888ዓ.ም (1896)የአድዋ ድል እንደሆነ አያጠራጥርም።

ይህ እንዳለ ሆኖ የህብረተሰቡ አባላት የሆኑት መምህራን ማህበራቸውን ኢመማን የመሰረቱት በ1941 ዓ.ም በየካቲት ወር ነበረ።የካቲት ለኢትዮጵያ መምህራንና ለማህበራቸው ኢመማ ልዩ ስፍራ አለዉ። በ1966ቱ የሥርዓት ለውጥ ዋዜማ ላይ መምህራን የራሳቸውን መብትና ጥቅም ማስከበር ጋር በተጓዳኝ ያቀረቧቸው ጥያቄዎች የሕዝቡን ብሶት አካተው ስለነበር አጋርና ደጋፊያቸው የበዛ ሆኗል። ከየካቲት 11ቀን 1966 ዓ,ም ጀምሮ ከወር በላይ የዘለቀው የመምህራን አገር አቀፍ የሥራ ማቆም አድማ በሲቪክ ማህበራት የመብት እንቅስቃሴ ታሪክ ትልቅ ሚና የነበረው ነው።



P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

በሂደቱም ባቀረቧቸው ጥያቄዎች ሕዝባዊ አመጽ ( አብዮት) በማስነሳት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። ታሪክ የካቲት ወር ጋር አያይዞ ለኢመማና ለአባላቱ የሚገባቸውን ስፍራ እንደሚሰጥ ይታመናል።

የኢትዮጵያ መምህራንና ማህበራቸው ኢመማ በአሁኑ ወቅት ያሉበት ሁኔታ እጅግ አደገኛና አሳሰቢ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋል።መምህራን በሐቀኛው ማህበራቸው ጥላ ስር ተሰባስበው የሙያና የዜግነት ግዳጃቸውን እንዳይወጡ የስርዓቱ ሕገወጥ ተግባራት ለከት የለሽ ሆነውባቸዋል። ማህበራቸው ተለጣፊና የፖለቲካ ክንፍ ለሆኑ ሆድ-አዳሮች ተሰጥቷል።የሙያው ክብርና ምገስ ረክሷል። ባለሙያዎቹ እንደ የዕለት ጉልበት ሠራተኛ (ኩሊ) የሥርዓቱ ባለሥልጣናትና ካድሬዎቻቸው ያዋክቧቸዋል፤ ሥነምግባር የጎደለው እርምጃ ይፈጸምባቸዋል፤የማያምኑበትን የፖሊቲካ አጀንዳ እንዲያራምዱ ይገዳዳሉ፤ የአካዳሚክ ነፃነት ከት/ቤት ቅጥር ግቢ ደብዛው ጠፍቷል። ከሁሉም በላይ መምህራንና ኢመማ የሚታገሉለት የትምህርት ጥራትና ለሁሉም የአገሪቱ ዜጎች በእኩልነት መዳረስ በከፍተኛ ደረጃ ዘቅጧል።ለዚህ ውድቀት ዋቢ የሚሆን በኮሌጅና በዩኒቨርስቲ ደረጃ የተመረቁ ወጣቶች የድንጋይ ፍልጥ (ኮብልስቶን) አምራች ሆነው መሰማራታቸውና የተማሩበት የትምህርት ዘርፍ ለአገር ግንባታ ሳይውል መቅረቱ ነዉ። እንዲሁም ሆሄያት ሳይለዩ ወደ አምስተኛ ክፍል የሚደርሱ ሊጋ ሕፃናት የምናይበት የትምህርት ፖሊሲ ከመሰረቱ የተናጋ መሆኑን ያመለክታል። በየካቲት 1966ዓ.ም የታየው የመምህራን የስራ ማቆም አድማ መንስኤው የመምህራን የደመወዝ ስኬልን ያካተተ ቢሆንም በዋናነት ተቃውሞውን ያጎለበተው የትምህርት ዘርፍ ክለሳ (Education Sector Review) የተባለው ነበር። ይህ ፕሮግራም (ፖሊሲ) መምህራን፣ ወላጆች፣ ተማሪዎች፣ ሌሎችም ባለድርሻዎች(Stake holders) ያልተሳተፉበት ከውጪ አገር በመጡና በሙያው ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ባልነበራቸው የአገር ውስጥ ምሁራን በዓለም ባንክ የገንዘብ እርዳታ በዚያን ወቅት የነበረውን የምዕራባውያን ፍላጎት ሊያንጸባርቅ በሚችል መልኩ የተዘጋጀ ስለሆነ በመምህራን ተቃውሞ ተግባራዊ አልሆነም። ከአመታት ጉዞ በኋላ ወያኔ/ኢህአዴግ የትምህርት ፖሊሲ ሲቀርጽ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት (መምህራን፣ ወላጆች፣ ተማሪዎችና ሌሎች ባለድርሻዎች) ያልተሳተፉበት፣ ውስጡ በተንኮል የተተበተበና በዘፈቀደ የተዘጋጀ ስለሆነ አንድ ትውልድ ተመራማሪና አምራች እንዳይሆን ተፈርዶበታል፤ፖሊሲው ትውልድ ገዳይ የሚል ቅጥያም ወጥቶለታል። ካለፉት መንግሥታት በባሰና በአስከፊ ሁኔታ መምህራን የስቃይ ኑሮ እንዲገፉ ተደርገዋል። በነፃነት የመደራጀት መብታቸው ተነፍጓል፣ ስለትምህርቱ በተለይ ስለአገራቸው ጉዳይ ባጠቃላይ መክረው ብሔራዊ ግዴታቸውን እንዳይወጡ የቁም እስር ሆነዋል።ይህ እንዳለም ሆኖ የኢትዮጵያ መምህራን ዛሬም እንደትናንቱ መብቶቻቸውን ለማስከበር፣ የትምህርቱን ጥራት ለማስጠበቅ፣ የአገራቸውን ሕልውናና የሕዝቡን ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ እየታገሉ መስዋዕትነትም እየከፈሉ ይገኛሉ። የማህበራቸውን የኢመማን 67ኛ ዓመት የምስረታ በዓል በዚሁ በየካቲት ወር በአደባባይ በነፃነት ማክበር ባይችሉም በየግል የሕሊና አዳራሻቸው ይዘከሩታል።በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ለኢመማ 67ኛ ዓመት ምስረታና ለ119ኛው ዓመት የአድዋ ድል በዓል እንኳን አደረሳችሁ ይላል። እንዲሁም በኢትዮጵያ የታሪክ ሂደት ውስጥ በየካቲት ወር የተፈጸሙትን እውነተኛ ገጽታዎችን ጠብቀን ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ የሁሉም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ግዴታ መሆኑን ማህበሩ ያሳስባል። የአድዋ ድል ለአፍሪካውያን ሁሉ ክብር ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ እላይ በመግቢያው ለመጥቀስ እንደተሞከረው የካቲት ሌላም ገጽታ አሳይቶናል። ወያኔ ጫካ የገባበትን የካቲት 11/1967ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነፃነት የሚያደርገው የትግል አካል አስመስሎ ለማሳየት ስብከቱ በበዓል ጋጋታ ታጅቦ እንዲስተጋባ እየተሠራ ነው። ወያኔ በሚቆጣጠረው የሚዲያ ዘርፍ( በቴሌኮም) አማካይነት በሞባይል ስልክ ለሕዝብ ለወያኔው 40ኛ ዓመት ምስረታ በዓል እንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ሲያስተላልፍ ከሕዝብ ለምን ለ119ኛው የአድዋ ድል በዓል እንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አታስተላልፉም ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ የኔትዎርክ ችግር ነው የሚል የለበጣ መልስ ሰጥቷል።ከዚህ ጸረ-አገርና ጸረ-ህዝብ ከሆነው ድርጅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገኘው አንዳች በጎ ነገር የለም። በተቃራኒው የዘር መድሎ፣ የአገር ሉዓላዊነት መደፈር፣ የታሪክ ብረዛ ፣ የባህልና የቅርሳቅርስ ውድመት፣ የመሬት ቅርምት፣ሙስና፣ ጉቦ፣ ግድያ፣ የዘር ማጥፋት፣ ስርቆት፣ የፍትሕ መዛባት መንሰራፋቱ ነው ሐቁ ።የእኛና የነርሱ የካቲት ለየቅል ምንለዉም ለዚህ ነው።የየካቲት ገጽታዎች ይህን ሁሉ ያሳያሉ።ወጣም ወረደ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ሠሪ ነዉ፤ ታሪኩን ቀጥረኞች ሳይሆኑ ሐቀኛ ልጆቹ ያጠናቅሩታል። ያኔ የየካቲት ትክክለኛ ገጽታ ጎልቶ ይወጣል። ይህ እንዲሆን ሁላችንም ጠንክረን እንታገል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

ድል ለኢትዮጵያ መምህራንና ኢመማ!!